www.ethiopianorthodox.org

# የፋሲካ ምንባብ

ትርጉም በመ/ር ኃይለማርያም ላቀው

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ከኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ሊቃውንት መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሹ ነው:: ከዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ቀደም ብሎ የተነሣውና በትምህርት፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ስልቱ፣ በቅድስናውና በተጋድሎው በኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ገንኖ የሚኖረው አባ ጊዮርጊስ ከዐርባ በላይ ድርሰቶችንም ደርሷል:: ለመሆኑ የእኛ ሊቃውንት መልስ አሠጣጥ የሚታይበት፣ የዶግማና የታሪክ ዕውቀታቸው የሚፈተሽበት ሥራ አለ ወይ? የሚሉ ሰዎች አሉ:: እኛም አለ እንጂ፡ አሳምሮ መልስ የሚሰጥ በግሩም አቀራረብ፤ እየጠየቀ፣ አለማወቅን የሚያሳይ፡ በዚያውም ላይ ቅድመ ዘርዐ ያዕቆብ ያለው ትምህርታችን ከአሁኑ ጋር አንድ መሆኑን ታዩ ዘንድ ከአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች ታዋቂ ከሆነው ከመጽሐፈ ምስጢር ድርሰቱ ይህን ክፍል ብቻ አቅርበንላችኋል::ድርሰቱ ጠጣርና ጠንካራ በመሆኑ ለአንዳንድ አንባብያን ማስተዋልን መጠየቁ አይቀሬ ነው:: ይሁን እንጂ መምህራን ለትምህርታቸው ምእመናን፣ ለሕይወታቸው፤ ተመራማሪዎችም ለምርምር ሥራዎቻቸው እንዲያስቡት በወቅቱ የሚቀርበውን ይህን ክፍል አምሃ አድርገን አቅርበንላችኋል፤ የቅዱሱ በረከት በሁላችን ይደር፤ አሜን:: በልዕልና የልዑላን ልዑል፣ በቅድስናው የቅዱሳን ቅዱስ፣ በንጽሕናው ከንጹሐን ንጹሕ፣ በግርማው ግሩማንን የሚያስፈራ፣ በግዛቱ የገዥዎች ገዥ፣ በአስተሳሰቡ የጥበበኞች ጥበበኛ መጠኑን ይህን ያህላል፣ ስፋቱ ይህን ያህላል፣ የማይባል፤ የእግሩ መረገጫ በዚህ ነው የማይባል መድረሻው እስከዚህ ነው የማይባል፤ በየዕለቱ በሁሉ ቦታ ምሉዕ ሆኖ ተአምራትን በሚያደርግ በእግዚአብሔር ስም እንጀምራለን፤ ለዘላለም አሜን::

የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳሳት የሆነውን የልዮንን ዘለፋ እንናገር ዘንድ በደል የወዘወዘን ከስካር መፍዘዝ ነቅተን፣ ከክፉት እንቅልፍ ራሳችንን እናንቃ:: የሀገር ሁሉ እናት ቁስጥንጥንያ ስሕተት በተሞላ ጉድጓድ ውስጥ ወድቃለችና:: የሮሜ አብያተ ክርስቲያናት በቁስጥንጥንያ ላይ አልቅሱ:: በወርቅ ምሰሶዎች ያጸናት የመንግሥት አገር፣ ዛሬ ግን በሸንበቆ /በመቃ መስዬ/ ወደቀች የቤተ ክርስቲያን ሹማምንት በልዮን ላይ አልቅሱ፤ አንጥረኛ የጴጥሮስን ሃይማኖት ሰይፍ ያለ እሳት አቅልጦ ጵጵስናውን አርክሷልና:: የምስጢር ካህናት በቤተ መቅደስ ላይ አልቅሱ፤ የጴጥሮስ መንበር ተነዋውጧልና:: እንግደህ ውሾች በመሠዊያው አደባባይ የሚመላለሱ ሆኑ:: የምድር ነገሥታት ምእመናን በመርቅያን ላይ አልቅሱ:: ያለ አባቱ ነግሧልና:: የንጉሥ ልጅ ወዳዋለችና የመንግሥቱን ዘመን አረከሰ:: ይኸውም የእግዚአብሔር መንግሥት ነው:: በልዮን ሃይማኖት ተባብሯልና:: ጠቢቡ በመጽሐፈ ጥበብ በእነዚህ በሦስቱ አገር ትነዋወጣለች:: ባሪያ ሲነግሥ፣ ሴት እመቤቷን ስትገፋ፣ ስታቃልል እና ሴት ደግ ሰውን [illegible] እውነት ነው:: መንበር በማ[illegible] በሆነ በመርቅያን መንግሥት ዘመን በእውነት አገር ተነዋወጠች:: የአንጾኪያ ንጉሥ ልጅ አስቀድማ የገባችውን ግብጻዊ የፈረሶች እረኛ አግሪጳን በአባቷ መንግሥት ላይ አስቀመጠችው:: እርሱ ለሠይጣን እየጠነ ለኢጋንንት እየሰዋ በአምልኮተ ጣዖት ዓለምን አረከሳት:: አብያተ ክርስቲያናትን አፍርሶ አብያተ ጣዖታትን ከፈተ:: ዳግመኛም የቁስጥንጥንያ ንጉሥ ልጅ መርቅያንን አግብታ በአባቷ መንበር ላይ አስቀመጠችው:: እርሱም አስቀድሞ በንስጥሮስ ሃይማኖት በኋላም በልዮን ሃይማኖት፣ አብያተ ክርስቲያናትን አረከሰ:: ለንስጥሮስና ለልዮን ከአካላቸው አለመገረዝ ይልቅ፤ የልባቸው አለመገረዝ ይከፋል:: ነቢዩ ኤርምያስ የአካላችሁን ሸለፈት ከምትገዘሩ ይልቅ የልባችሁን ሸለፈት ግዘሩ እንዳለ::

ሊቀ ጳጳሳት ልዮን ዛሬ የተሳሳቱ ሰዎች አለቃ ሆነ:: በማይገባ የመንግሥት ወንበር ላይ የተቀመጠ መርቅያንም፤ የገዳማትን አድባራትንና አብያተ ክርስቲያናትን አርክሶ የማይገባ ሃይማኖትን ገዛ:: በሁለት መንገድ ለክርስቶስ መገዛትን በምታዝ የደብዳቤ መጽሐፍ ትስብእትን ሰውነትን ዝቅ አድርጎ መለኮትን ከፍ ያደርጋል:: ከወንጌል ቃል መንፈስ ያድናል፤ ሥጋ ግን የሚጠቅመው የለም የሚለውን ምክንያት አደረገላቸው:: ይህን ቃል መንፈስ ያድናል ስለመለኮት አለ ተናገረ ሥጋ ግን የሚጠቅመው የለም፤ የሚለውን ስለ ትስብእት አለ ተናገረ ብለው ተረጐሙት::

የእፉኝት ልጆች መለካውያን ንጉሣውያን ሆይ፤ መለኮት ግን ለብቻው የሚያድን ከሆነ ለምን የእግዚአብሔር ልጅ ከማርያም ሰው ሆነ:: መለኮት ያለ ሥጋ ብቻውን የሚያድን ከሆነ ስለእናንተ የሚፈተት ለብዙኃን ቤዛ የሚሰጥ ሥጋ ይህ ነው:: እንካችሁ ብሎ ለምን አለ? መለኮት ያለ ሥጋ ብቻውን የሚያድን ከሆነ ሥጋዬን የበላ ስለ እኔ ሕያው ይሆናል፤ ደሜንም የጠጣ ሞትን አይቀምስም ለምን አለ? መለኮት ብቻውን ያለ ሥጋ የሚያድን ከሆነ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ነው ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና ለምን አለ? መለኮት ብቻውን ያለሥጋ የሚያድን ከሆነ አብ ሕያው እንደሆነ፤ እኔም ስለ አብ ሕያው ነኝ:: ሥጋዬን የሚበላ ስለ እኔ በሕይወት ይኖራል ለምን አለ? መለኮት ብቻውን ያለ ሥጋ የሚያድን ከሆነ እኔና አብ አንድ ነን ስለምን አለ? መለኮት ብቻውን ያለ ሥጋ የሚያድን ከሆነ ኦሪት ያገለገሏትን ነቢያት ለምን አላዳነቻቸውም? ኦሪት ግን እግዚአብሔር ሰው ሳይሆን የተነገረች የመለኮት ንባብ ናት:: ስለዚህም ጳዉሎስ በሙሴ ሕግ ኦሪት መጽደቅ በተነሣ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴት ተወለደ:: ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ አለ እግዚአብሔር በመለኮቱ ባለመድኃኒት ነው:: በሰውነቱ በትስብእቱ የድውያን ፈውስ ነው:: ባለ መድኃኒት ከእርሱ ጋር ፈውስ ከሌለ ምን ያደርጋል?

ድውያን በሚድኑበት ገንዘብ ባለመድኃኒት የፈውስ ዕፅንም ካላዘጋጀ ምን ይጠቅማል? ባለ መድኃኒቱ በታመሙ ሰዎች ልጅ ዘንድ አደረ:: ለድውያን ፈውስ ከሚሆንበት ገንዘብ ከእርሷ ምድራዊ ሥጋን ነሥቶ ከመለኮቱ ጋር አንድ አደረገው:: ባለመድኃኒት ከሰማየ ሰማያት መጥቶ ወርዶ የፈውስ ዕፅ በዳዊት ቤት ተገኘ:: ባለመድኃኒቱ ያለ መለኮትና ትስብእት መዋሐድ ፈውስ እንደማይሆን ዐወቀ:: ስለዚህም ራሱን ሰው ለመሆን አሳልፎ ሰጠ:: ድውይ ግን ለራሱ ፈውስን ያደርግ ዘንድ አይችልም:: ነገር ግን ባለመድኃኒቱን ፈውስን በሚያገኝበት ገንዘብ ሁኔታ መድኃኒት ያደርግለት ዘንድ ይለምነዋል:: ዳዊት ድውይ ነኝ እና አቤቱ ይቅር በለኝ፤ [illegible] ከዋልና ፈውሰኝ ብሎ ለመነ:: ነቢዩ በአርዮን ሚስት ውበት በዲያብሎስ ጦር ተነድፎ እንደ ቆሰለና አጥንቶቹም ሰይጣን በቀሰቀሰው የዝሙት ጸር ዝሙትን በመጎምጀት እንደ ታወኩ ዐወቀ:: ባለመድኃኒት ልመናውን ተቀበለ:: ከዱር ዕፅዋት ወይም ከገነት ዕፅዋት ፈውስን አልፈለገለትም:: በሚድንበት ገንዘብ መድኃኒትን በእንስሳትና ወይም በዱር አራዊት ደም አላደረገለትም:: ከወገቡ በወጣች በመዋለጃ ዘር በዝሙት ጸር በነደፈችው በኦርዮ ሚስት በቤርሳቤሕ ማኅፀን ተወስኖ ፈውስን አደረገለት እንጂ:: ዳግመኛም ይህች የመዋለጃ ዘር ከኃጥኣን ወገብ ወጥታ፣ በኃጥኣን ማኅፀን ውስጥ ተቀምጣለች:: ከኦርዮ ሚስት ከዳዊት ልጅ ከሰሎሞን ዘር ጀምሮ እስከ ኢያቄምና ሐና ልጅ ማርያም ድረስ እንግዲህ ከልጅ ልጆች ከትውልድ ትውልድ የምትወጣ ሆነች:: ይህች ግን በወንድና ሴት ፈቃድ በመዋለጃ ዘር ተወለደች:: እርሷ ግን በፍጹም እንዳትረክስ መንፈስ ቅዱስ ጠበቃት:: የእግዚአብሔር እናት ትሆን ዘንድ አላትና ደስተኛ ይሆን ዘንድ ንጉሡ ከመግባቱ አስቀድሞ አዳራሹን እንደሚያስጌጡት::

እግዚአብሔር ሙሴንም ከማይነቅዝ እንጨት ታቦትን ለራስህ ሥራ፤ በውስጥና በውጭ ወርቅ ትለብጠዋለህ፤ በውስጧም የምሰጥህን ሕግ ታኖራለህ አለው:: እግዚአብሔር ለሙሴ በሰማይ ጽላተ ኦሪትን ከመስጠቱ አስቀድሞ ለመቀመጫዋ ታቦትን ያዘጋጅላት ዘንድ አዘዘው:: እንዲሁ ድንግል ማርያም በቅድስናና በንጽሕና ትሸለም ዘንድ አዘጋጃት:: ውስጧም ያለው በይውሕናና በልቡና ውጭዋን ያለው መንፈስ ቅዱስን የሚያድሳት በጾም በንጽሐ ሥጋ መኖሯን የሚያመለክት ነው:: የምሰጥህ አለ፦ በውስጧም ትኖራለህ ያለው:: ይህም የእግዚአብሔር ትእዛዝ በሰማይ ጽላት ላይ እንደ ተጻፈ እንዲሁም የአባቱ ትእዛዝ በወልድ ሕሊና ውስጥ የተሳከ ነው::

ባለመድኃኒት በኃጢአት ጦር ወደ ታመመ ወደ ዳዊት ቤት መጣ:: በልጁ ማኅፀን አድሮ መድኃኒትን አደረገለት:: ከእርሷ በነሣው ሥጋ ቁስሉን ፈወሰው፤ ባለመድኃኒቱ ከአብ ዘንድ ከጽርሐ አርያም መጣ:: ስሟ ጽዮን በተባለ በዳዊት አገር መድኃኒት ተገኘች:: ለእስራኤል ከጻድቃን መድኃኒትን ማን ይሰጣል:: የተባለው ትንቢት ተፈጸመ:: የሚያድን መንፈስ ነው:: ሥጋ

www.ethiopianorthodox.org

ግን የሚጠቅመው የለም፤ ያለው ቃል
ትርጉም ግን የአዳም ሥጋ ለልጆቹ ድኅነት
አልጠቀመም በእርሱ ላይ የመለኮት ጭማሪ
የለምና ከመሬት ወጥቶ ወደ መሬት
ገብቶአልና:: እንዲሁ የልጆቹም ሥጋ ለራ
ሳቸው ወይም ለባዕድ ጠቃሚ አልሆ
ነም:: ሕያውና ማኅያዊ ከሚሆን ከመለ
ኮት ኃይል አልተደመረምና:: የእግዚአብሔር
ልጅ ሥጋ ግን በመለኮቱ ጠቃሚ ነው::
መለኮቱም በሥጋዌው ጠቃሚ ነው::
በሥራ ሌላውን እንደሚረዳው አይደለም::
በማትለያይ በአንድ ጽምረት በማትዋዋስ
በአንዲት ህላዌ በማይናወጥ በአንዲት
ባሕርይ በማይጐድል በአንዲት ዕሪና ያለ
ነው እንጂ:: ሰው ግን በፈቃዱ እግዚአ
ብሔርን መሆን አይችልም፤ እግዚአብሔር
ግን በፈቃዱ ሰው መሆን ይችላል:: እግዚ
አብሔር በተዋርዶ ሰው መሆን ቢችልም
ዳግመኛ ሰው መሆኑን በልዕልና እግዚአ
ብሔር ወደ መሆን ይመልሰው ዘንድ ይችላል::

ክዋኔው ግን ወደ መለኮት ግዕዝ በጠባይ
መመለስ አይደለም:: በባሕርይም ወደ ሰው
ልጅ ግዕዝ ጠባይ በመለወጥ አይደ ለም::
መለኮትም ከመውዛት፣ ከድካም ከረሐ
ብና ጥም፣ ሕማምና ሞት ከመቀበል ሳይ
ነካ፣ ትስብእትም የሰው ልጅን ሥርዓት
ከኃጢአት በስተቀር በአንድ አካልና በአንድ
ባሕርይ ሳያቦዝን ነው:: ከትስብእቱ መለ
ኮቱ አልሰለጠነም፤ ከመለኮቱ ውሕደት
ድማሬ ትስብእቱ አልሰለጠነም፤ እግዚአ
ብሔር ሰው ሆነ ሰው ግን እግዚአብሔርን
መሆን አልቻለም፤ ከኩነት በኋላ በሰማ
ያት ካለው ከአባቱ ዘንድ ክብሩን አልተ
ወም:: ከመለኮቱ ጋር አዛምዷት ከእናቱ
ዘንድ ሥጋዌን አልተወም::

የልዮን ሰው ሆይ ትስብእት ከመለኮት
ያንሣል ትላልህ? ከመለኮቱ ትስብእቱን አሳ
ንሣችሁ አምልኮት ካደረጋችሁ እነሆ እና
ንተ ባለ አራት ትባላላችሁ:: ባለ ሦስት
አይደላችሁም:: አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ
በሦስትነት ትክክል ናቸው:: የወልድ ትስ
ብእት ግን ከመለኮቱ ጋር ትክክል አይደ
ለም፣ ስትሉ ከመለኮቱ ጋር አንድ አልሆ
ነም፤ ስትሉ እነሆ ወደ ሁለት አካል ከፈላ
ችሁት:: አንዱን ለማሣነስ፣ አንዱን ለማ
ብዛት አደረጋችሁ:: እነሆ እናንተ ካልተ
ጠመቁት ከንዑስ ክርስቲያን አንሣችሁ
የሰይጣን መከፈልት ሆናችሁ:: ከክርስቶስ
መንጋ በጐች ተከፈላችሁ:: አዳምም ከእኛ
እንደ አንዱ ሆነ የሚለውን የአሪት ቃል
አፈረሳችሁ:: እንደ ኪሩቤልና እንደ ሱራ
ፌል አሳለም:: እነርሱም ግን ፍጡራ
ናቸውና ከእኛ እንደ አንዱ አለ እንጂ፤
ከአዳም ልጅ ሥጋን ከነሣው ከወልድ ዋሕድ
በስተቀር ከሥላሴ አንድ ማነው? እነሆ ትስ
ብእት ዕሪና ከመለኮት ጋር ተገኘ:: ዳግ
መኛም በወንጌል ፊልጶስ ጌታ ሆይ አብን
አሳየንና ይበቃናል ባለው ጊዜ እርሱም ፊል
ጶስ ይህን ያህል ዘመን ከእኔ ጋር ስትኖር
አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶ
አል አለ:: እነሆ እኔን ያየ አብን አየ ባለ
ጊዜ ወልድ ትስብእቱን ከአባቱ መለኮት
ጋር ያስተካክለዋል ከትስብእቱ በስተቀር
ወልድን ያየው ማን ነው:: የአብ መለኮት
እንዳልታየ መለኮቱ ግን አልታየም:: የአብ
ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሕልውና ግዕዝ
አንድ ነውና:: ትስብእቱን ስለ ተመለከተ
የአባቱን መለኮት ከመመልከት ጋር አስ
ተካከለው፤ መለኮቱ ግን እስከ መቼም
የሚታይ አይደለም:: ዳግመኛም ከሰማይ
የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ አለ::
ያለ ሥጋው በስተቀር መለኮት ኅብስት ይባ
ላልን ሥጋዬም እውነተኛ መብል ነው ብሏልና::

ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በስተ
ቀር ወደ ሰማይ የወጣ የለም ብሏልና::
የሰው ልጅ ግን ከሰማይ እንደ ማይወርድ
እናውቃለን:: ኃይልን ከሥጋዌ፣ ሥጋዌን
ከኃይል እንዳንለይ የመለኮትን ወደ ትስ
ብእት መውረድ ቆጠረው እንጂ:: እነሆ
ወደ ዚህም የትስብእት እሪና ከመለኮት ጋር
አልተለየም:: ጳዉሎስም እርሱ በእግዚ
አብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር
ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር
አልቆጠረውም፤ ነገር ግን የባሪያውን መልክ
ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደረገ::
በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋ
ረደ:: ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት
እንኳ የታዘዘ ሆነ:: በዚህም ምክንያት እግ
ዚአብሔር ዳግም ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደ
ረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም
ሰጠው:: ይህም በሰማይና በምድር ከምድ
ርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም
ይንበረከኩ ዘንድ፤ ምላስም ሁሉ ለእግዚአ
ብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ
እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው አለ:: እነሆ
ጳዉሎስ እኔን ያየ አብን አየ ያለውን አንድ
ወልድ ቃል ሥጋዌውን ማየት የአብን
መለኮት እንደማየት እንደሚቆጠር ደገመ::
ጳዉሎስም የወልድን የሥጋዌ መልክ ወደ
አብ መልክ አርአያ እያሳየ እርሱ በእግዚ
አብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር
ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር
አልቆጠረውም:: ነገር ግን የባሪያውን መልክ
ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደ
ረገ፤ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት
እንኳ የታዘዘ ሆነ ብሏልና::

ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀ
ማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም ያለው
ስለ ሰውነቱ እንደሆነ ዕወቅ:: መለኮቱ ግን
ከዓለም አስቀድሞ እግዚአብሔር ነው:: ዓለ
ምንም በፈጠረ ጊዜ እግዚአብሔር ነው::
በሥጋዌው እግዚአብሔር ነው:: ስለ ትስ
ብእቱ እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር
ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀ
ማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፤ አለ::
የትስብእትን እግዚአብሔር ወደ መሆን መነ
ጠቅን ይናገራል:: የእግዚአብሔር ሰው ለመ
ሆን መዋረድ በአምልኮት ትክክል ይሆን
ዘንድ ነው:: የሚጠፋ ሥጋን ለበሰ:: ይህን
የሚጠፋውን ሥጋ የማይጠፋ አደረገው::
ይህን የሚሞተውን ሥጋ ከማይሞት ሕል
ውና ጋር ይተካከል ዘንድ የማይሞት አደ
ረገው:: ምድራዊ ሥጋን ለበሰ:: ይህ ምድ
ራዊ ሥጋ ከእርሱ ልዕልና ጋር ትክክል
ይሆን ዘንድ ሰማያዊን አደረገው:: የመ
ከራ ሥጋን ለበሰ ይህን የመከራ ሥጋ ደካ
ማው ከእርሱ ኃይል ጋር ትክክል ይሆን
ዘንድ ለክብር አደረገው:: የሚታመም
ሥጋን ለበሰ ይህ ምድራዊ ሥጋ ከእርሱ
ልዕልና ጋር ትክክል ይሆን ዘንድ ሰማያ
ዊን አደረገው:: የመከራ ሥጋን ለበሰ ይህን
የመከራ ሥጋ ደካማው ከእርሱ ኃይል ጋር
ትክክል ይሆን ዘንድ ለክብር አደረገው::
የሚታመም ሥጋን ለበሰ ይህን የሚታመ
መውን ሥጋ ከማይታመም ባሕርዩ ሕላዌው
ጋር ትክክል ይሆን ዘንድ የሚታመም አደ
ረገው:: እንዳይለያይ በጽምረት አዋሐደው
እንዳይጨምርም በመጠበቅ በተአቅቦ አኖ
ረው:: የተደመረው የተዋሐደው ጠባይን
በማስወገድ አይደለም:: ሰው የሆነውም በመ
ለኮት መለወጥ አይደለም:: በትንሣኤው
ጊዜ እንደ ኢያኢሮስ ልጅ ጣቢታ ተነሽ
ብሎ የሥጋውን በድን አልጠራም:: እንደ
ወልደ መበለትም፤ የአልጋውን ሸንኮር
አልዳሰሰም፤ ዳግመኛም እንደ አልዓዛር
ተነሣ፤ ወደ ውጭ ውጣ ብሎ አልተጣራም::
ከፈጣሪ ዘንድ የፍጥረት ሥራ አገልጋይ
እንዳይሆን:: አንዱ ፍጡር፣ አንዱ ፈጣሪ፣
አንዱም ይበልጣል፣ አንዱም ያንሳል እን
ደሚሉ እንደ መለካውያን አምላኮችን እን
ዳናከፋ::

ሰነፎች የሮሜ ታላላቆች ሆይ እግዚአ
ብሔር ከጐሰቆለች ሥጋችን ጋር
ፍን ካላፈረ ሥጋዌን ከመከራ ከፍ ማድረ
ግና ከመለኮቱ ጋር መስተካከልን እንዴት
ያፍራል? ትስብእቱንም በመለኮቱ ክብር
ያሳትፋት ዘንድ ካልፈቀደ መለኮቱን በት
ስብእቱ ኃሳር ባያሳትፈው ከቡሩን መከራ
መሸከሙ ያስደንቀዋል:: ለጎሰቆለው ክብርና
ምሥጋና መሸከም አይደነቅለ ትም:: ዳግ
መኛም ሕያውን ሕማምና ድካም በመሸከሙ
ያስደንቀዋል:: ሕመምተኛው የዘላለም ሕይ
ወትን መሸከሙ አይደነቅለትም:: እግዚአ
ብሔር የመለኮቱን ክብር ወደ ሥጋዌ ኀሳር
መከራ ማውረዱ ካላስደነቀው ሥጋዌውን
ወደ መለኮቱ ክብር ከፍ ማድረጉ እንዴት
ያስደንቀዋል::

የሮሜ ሰዎች ሆይ የተደሰታችሁትን ያህል
ትተክዛላችሁን? የተደሰታችሁትንስ ያህል
ታዝናላችሁን? እግዚአብሔር የሰውን ልጅ
ወድዶ የእኛን ሥጋ ከመለኮቱ ጋር ትክክል
አደረገው:: ሥጋዌውን ከመለኮቱ ጋር ስለ
አደረገው ለእግዚአብሔር ትተክዙለታላችሁ::
ሰማያትን ዝቅ አድርጐ ወደ ምድር በወረደ
ጊዜ፤ አቤቱ ወደ ደካሞች መከራ ለምን
አትውረድ አላላችሁም? የእኛን መከራ
እንዳትሸከም ወደ ሴት ድንግል ማኅፀን
አትመለስ ለምን አላላችሁም? የእግዚአ
ብሔርን ፈቃድ ማድከም ከቻላችሁ ለምን
ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በመሬታዊ ሰው
ትጠመቅ ዘንድ አትውረድ አትሉትም?
የእግዚአብሔርን ትሕትናውን ማስተንኀል
ከተቻላችሁ ዳግመኛ የእግዚአብሔርን ፈቃድ
መከልከል ብትችሉ በጲላጦስ አደባባይ ላይ
አትቁም የመስቀል ኃፍረትን አትቀበል
ለምን አትሉትም:: እንደገናም በፍርድ ቦታ
መሰቃየት ይሻለናልና:: ስለ እኛ ከሞት
በፍርድ ቦታ መሰቃየት ይሻለናል:: የሞ
ትን ጽዋ ስለ እኛ አትጠጣ ለምን አትሉትም?

እኔ ግን ስለ እናንተ እላለሁ፤ በእርሱ
ሞት የሕይወትን ተስፋ ከምታገኙ ይልቅ
በፍርድ ቦታ መቀመጥ ይሻላችኋል? እንደ
ልባችሁ ፍላጐት አግኙ:: መለኮቱን መከራ
ከመቀበል መከለከል ከተቻላችሁ ሥጋዌውን
በመለኮት እሪና ክብርና ድካም ከመቀበል
መከልከል እንዴት ትችላላችሁ? እኔ ግን
ማርያም ለእርሷ መድኃኒትና ለእኔ መድ
ኃኒትነት ትወለድ ዘንድ ሔዋኝ እንኳን
ከተከለከለው ዕፅ በላች እላለሁ:: ሔዋን
በትእዛዘ እግዚአብሔር ተጠብቃ ብትኖር
ብቻዋን ከባለቤቷ ጋር በገነት ፍሬዎች
እየተደሰተች በተቀመጠች ነበር:: ፍዳዋን
ለማስቀረት ከዘሮቿ ዘር ድንግል ማርያምም

www.ethiopianorthodox.org

ዲያብሎስ መርዝም በልጅ ልጅ በመለኮት ጨው ባልተላሰ፤ ዳግመኛም አዳምን ከገነት ያሳደደ የእግዚአብሔር ልጅ አዳምን ወደ ገነት ይመልሰው ዘንድ እላለሁ:: አዳም ከገነት ባይሰደድ የእግዚአብሔር ልጅ አዳምን ወደ ገነት ይመልሰው ዘንድ በዕፀ መስቀል ላይ እጆቹን ባልዘረጋ፤ አዳም በገነት ቢቀመጥ ግን መድኃኒታችን ከማርያም ባልተወለደ:: በተድላ ገነት ውስጥም የመዋለጃ ዘር ባልሆነ፤ በውስጧ የሚያድሩ በሰማይ ሥርዓት ይኖራሉና:: በገነት አጸድ የወንድና ሴት ግንኙነት ሩካቤ የሚገባ ቢሆን አዳም ሔዋንን ባወቃት ነበር:: በዚያ ለሰባት ዓመት ያህል ተቀምጠዋልና:: የገነት አጸድ ግን የቅዳሴ ቦታ ነውና በውስጧ የሥጋና ደም ሕግ ያደርግ ዘንድ አይቻልም::

በገነት ውስጥ ግን ለሰባት ዓመታት ያህል እንደ ተቀመጡ ለሙሴ የፊት መልአክ እንደ ነገረው በመጽሐፈ ኩፋሌ ይገኛል:: አዳም ከሔዋን ጋር ከገነት ከወጡ በኋላም ሳይቀር ግንኙነት ግን አላደረጉም:: እኛም በሥጋ የእግዚአብሔር ዘመድ ባልሆንን:: ሰነፉ ሆይ እግዚአብሔር አዳምን ሳይፈጥረው አስቀድሞ ትዕዛዙን ተላልፎ የተከለከለውን ዕፀ እንደሚበላ የማያውቅ ይመስልሃልን? እግዚአብሔር ከአዳም ኃጥአን እንደሚወለዱ ካላወቀ፣ ለምን ፈቃዱን ለማያደርጉት ማደሪያ ይሆናቸው ዘንድ ገሃነምን አዘጋጀት? ጻድቃን ከአዳም እንደሚወለዱ ካላወቀ ለምን ትእዛዙን ለጠበቁ ርስትን ትሆናቸው ዘንድ ተድላ ገነትን አዘጋጀት?

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ከመፍጠሩ አስቀድሞ ትእዛዙን በመተላለፍ እንደሚበድል አውቋል:: ስለዚህ ሰው ከታናሽነቱ ጊዜ ጀምሮ በልቡ ውስጥ ተንኰል ተሹሟልና አለ:: ዳግመኛ እግዚአብሔር ከአዳም ልጅ ተወለደ፤ ከእርሷ የነሣውን ሥጋ ከመለኮቱ ጋር ትክክል እንደሚያደርገው አወቀ:: ስለዚህ አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ አለ:: እነሆ እጁን ከፍ አድርጐ ከዚህም ዕፀ ሕይወት በልቶ ለዘላለም ይኖራል:: እነሆ ትስብእት ከመለኮት ጋር ትክክል እንደሆነ ታወቀ:: አስቀድመን እንደ ተናገርን ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረ ውም:: ነገር ግን የባሪያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደረገ:: በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ:: ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ ብሎ ምስክር እንደሆነ ታወቀ::

[illegible] እንዳልተያዘ ዕወቅ:: ስለ ትስብእቱ ሐዋርያው ይህን አለ:: ከዚህም በማስከተል በዚህም ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለልክ ከፍ ከፍ አደረገው፣ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው አለ:: የወልድ ትስብእቱ ከመለኮቱ ጋር ትክክል ካልሆነ ግን ጳዉሎስ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ የክብር ጌታ እንደሆነ ይል ዘንድ እንዴት ተባለ? እነሆ የወልድን ሰውነት ከፈጣሪ መለኮቱ ጋር አሳየው:: ገብርኤልም ልጅን ትወልጃለሽ ብሎ ባበሠራት ጊዜ መለኮትን ትወልጃለሽ አላለም:: የመለኮት ትስብእትን ጉዳና በአንድ መልክ ሲያሳይ ልጅን ትወልጃለሽ አለ እንጂ:: ድንግልም በወለደችው ጊዜ እንደ ትንሽ ልጅ እንደ ሕፃናት ሥርዓት እንዳይጮህ በሁለት ወገን በማኅፀኗ የተቀመጠ አይደለም:: መለኮቱ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍም በሁሉ ቦታ ምሉዕ ሆኖ የክብር ኃይል እንደ ተለመደው እንዳይጮህ በዚያ እርሱ ለዘላለም አባቷ ሆኖ ሳለ እናት ለመሆን ተገባችው:: ካለመኖር ወደ መኖር አምጪውም በሌለበት ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ ተወለደ:: በዚህም ከእርሷ የተወለደው እግዚአብሔር እንደ ሆነ ዐወቅን:: በመለኮት ውሕደቲ ካልሆነ በስተቀር ሰው ግን በተዘጋ በር መውጣት አይችልምና በከንዶቹ ታቅፎ በእጆቿ ተዳሰሰ:: በዚህም በእቅፍ የተቀመጠው እርሱ የሰው ልጅ እንደሆነ ዐወቅን፤ በዚህም የሕፃናትን ሥርዐት እንደ ሰው ልጅ የፈፀመ እርሱ እንደሆነ ዐወቅን፤ ከትስብእት ጽምረት በስተቀር እሳተ መለኮትን መዳሰስ የሚችል የለምና፤ ወንድ ከማታውቀው ከድንግል ጡቶች ወተት መነጨ:: ከዚህም ከእርሷ የተወለደው አምላክ እንደሆነ ዐወቅን:: ኮከሬብ ዐለት ውኃን ካፈለቀው በስተቀር ከድንግል ጡቶች ወተትን ማመንጨት የሚችል የለምና:: ዳግመኛም ብቻውን በድንግል ማኅፀን ካደረ ከእግዚአብሔር በስተቀር በድንግልና ወተት ያደገ የለም:: በአንድ ጉኑ አምላክም ሰውም ነው::

ዳግመኛም ትስብእት በዮርዳኖስ ወንዝ በትስብእት ሕግ በሰው ሕግ ለመጠመቅ አጐንብሶ የመለኮትን ውሕደት አሳየ:: አብም የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን



[illegible] ሆነ፡ ስለ መለኮቱ ሳይለይ ስለ አንዱ ምስክር ሆነ:: ስለ ትስብእቱም ሳይለይ በአንድ ጥሪ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ እንጂ:: ድንግል ከብቻዋ ሥጋዋ ከነሣው ሥጋ ጋር ከተዋሐደ መለኮት ያለ መለኮት ውሕደት ብቻዋን ሥጋዌን እንዳልወለደች እንዲሁ አብም ስለ ልጁ በመሰከረ ጊዜ ስለ ኃይለ መለኮቱ ሥጋዌን አልለየም:: በማዋሐድ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ እንጂ:: ለአባቱም አንድ ቢሆንም መለኮቱ ከሥጋዌው አልተለየም:: ለእናቱም አንድ ቢሆንም ትስብእቱና መለኮቱ አልተለያየም:: መለኮቱ ከትስብእቱ፣ ትስብእቱም ከመለኮቱ የዓይን ቅንድቦች ጥቅሻ ያህልና የዓይኖች ጥቅሻ መጠን ያህል ከገወን በኋላ አልሰለጠነም:: ስለ ሥጋዌውም ዳዊት፦ እግዚአብሔር አለኝ አንተ ልጄ ነህ፣ እኔ ዛሬ ወለድሁህ፣ ለምነኝ አሕዛብን ለርስትህ፣ የምድርን ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ:: እንግዲህ ዳዊት እስከ ምድር ዳርቻ ነግሦ ነበርን? የአሕዛብን ግዛት ርስት አድርጐ ሰጠውን? ግዛቱ ከይሁዳ ግዛት መስፍንነቱም ከኢየሩሳሌም አውራጃ አላለፈችም:: ይህን ስለ ወልድ ተናገረ:: የወልድ ሥጋው ከዳዊት ዘር ነውና ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ ለመሲኸዬም ለተቀባው መብራትን አዘጋጃለሁ፤ እንደ ተባለ:: በሌላም በኩል እግዚአብሔር ለዳዊት ማለ አይጸጸትም ከሆድህ ፍሬ በመንበርህ ላይ አስቀምጣለሁ ይላል:: ገብርኤልም ማርያምን እግዚአብሔር አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል አላት:: እንግዲህ ክርስቶስ በአባቱ በዳዊት መንበር ላይ መቼ ተቀመጠ? ከይሁዳ ንጉሥ ሄሮድስ ፍርሐት የተነሣ እናቱ ከቦታ ቦታ እያሸሸችው በችግር ያደገ አይደለምን?

ሰብአ ሰገል የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ:: ንጉሡ ሄሮድ ስም ሰምቶ ደነገጠ፣ ኢየሩሳሌምም ሁሉ ከእርሱ ጋር የካህናትንም አለቆች የሕዝቡንም ጻፎች ሁሉ ሰብስቦ ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው:: አንቺ ቤተ ልሔም የይሁዳ ምድር ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሽም፤ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና ተብሎ በነቢይ እንዲ ተጽፏልና በይሁዳ ቤተ ልሔም አሉት::

ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገልን በስውር ጠርቶ፤ ኮከቡ የታየበትን ዘመን ከእነርሱ በጥንቃቄ መርምሮ ባገኛችሁትም ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ፣ አላቸው:: እነርሱም ንጉሡን ሰምተው ሄዱ እነሆም፣ በምሥራቅ ያዩት ኮከብ ሕፃኑ ባለበት ላይ መጥቶ እስኪ ቆም ድረስ ይመራቸው ነበር:: ኮከቡንም ባዩ ጊዜ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው:: ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፤ ወድቀውም ሰገዱለት፣ ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅ ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት::

እነሆ አሕዛብ የአምላክን ልጅ ለመቀበል ለመንግሥቱ እጅ መንሻ በመስጠት ቀደሙ:: የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ፤ የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻ ያቀርባሉ የሚል ጽሑፍ እንደ ተጻፈ ዳግመኛም እርሱ ይኖራል:: ከዓረብም ወርቅ ይሰጡታል ሁልጊዜም ወደ እርሱ ይጸልያሉ፤ ዘወትርም ይባርኩታል የሚል ጽሑፍ ተጽፏል:: ከዚህ በኋላ ወደ ሄሮድስም እንዳይመለሱ የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ለሰብአ ሰገል ታያቸው እንዳዘዛቸው አድርገው በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው ሄዱ:: ሄሮድስ ሰብአ ሰገል እንደ ተሳለቁበት ዐውቆ እጅግ ተቆጣና ልኮ ከሰብአ ሰገል እንደ ተረዳው ዘመን በቤተ ልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን ሁለት ዓመት የሆናቸውን ከዚያም የሚያንሱትን ሕፃናትን ሁሉ ይገድሉ ዘንድ አዘዘ:: በንጹሐን ሕፃናት ላይ የሞት ፍርድ ከገሊላ ንጉሥ ከሄሮድስ አፍም ወጣ::

የአሕዛብ ነገሥታት በዕጣን ህብት ለክህነት፣ በወርቅ ህብት ለመንግሥቱና በከርቤ ህብት ለሥጋው ንጉሥ በሞት ፍርድ መታሰቢያውን ይሽር ዘንድ የሞትና የሕይወት ሥልጣን በእጅ ያለውን በሰይፍ እጅ ይነሣው ዘንድ ወደደ:: ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታይቶ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ:: ሕፃኑንና እናቱን ያዝና ወደ ግብጽ ሂድ አለው:: ዮሴፍም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ ግብጽ አገር ሄደ:: እነሆ እግዚአብሔር በቀላል ደመና ተጭኖ ወደ ግብጽ ይወርዳል፤ ግብጽን ያጥሉቀልቃታል፣ ጣዖቶቿንም ተብሎ በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ወደ ግብጽ ሄደ::

ሄሮድስም የሕፃኑን መኖሪያ ቦታ ባጣ ጊዜ በእርሷ ላይ ከፈሰሰው የሕፃናት ደም የተነሣ የገሊላ ምድር እስክትቀላ ድረስ ሕፃናትን ይገድል ዘንድ ጀመረ:: ልጆቻቸው ከተገደሉባቸው ሴቶች ጡቶች ከተንጠባጠበው ወተት የተነሣ ኑጭ የሆነ ቦታም አለ::

www.ethiopianorthodox.org

በገሊላ የዝናብ እንባ ፈሶ የልቅሶው ጩኸት እስከ ረጅሙ ወጣ:: ስለዚህ እግዚአብሔር የሄሮድስን ሞቱን አፋጠነው:: ለእንደዚህ ዓይነት አውሬ ምን ያህል የስቃይ ቅጣት ይገባዋል? ለእንደዚህ ዓይነት ክፉ ምን ያህል የገሃነም ስቃይ ይገባዋል? የልቡ ክፋት እንደ ሰው ልጅ የልብ ክፋት አይደለም ከአባብ ልብም በክፋት ይከፋል። ሕፃን አባብን በእጁ እንደ ያዘው ቢጫወትበትም በላዩ ላይ በእርሱ ላይ መተናኮል አይችልም:: በጥርሶቹም አይነክሰውም:: የሕፃኑ የየዋህነቱ ኀይል የእባቡን የልብ ክፋት ያሸንፋልና፣ ሄሮድስ ግን ጡት የሚጠቡ ሕፃናትን የእናታቸውን ጡቶች መከልከል አያሳዝነውም:: ወታደሮች አንገታቸውን ለማስቀላት አሳልፈው ሲሰጡአቸው እነርሱ ግን ለግድያ እንደሚሰጡአቸው ሳያውቁ በየዋሕነት ይስቁላቸው ነበር። ሁለተኛው ሄሮድስ ከነቢያት ሁሉ በሚበልጠው በዮሐንስ ደም በደልን ጀመረ:: በኋላም በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከሰቃልያን ጋር ተሳተፈ:: ወንጌላዊው እንደተናገረው ጲላጦስ ግን ገሊላ ሲሉ በሰማ ጊዜ፣ የገሊላ ሰው ነውን? ብሎ ጠየቀ:: ከሄሮድስ ግዛት እንደ ሆነ ባወቀ ጊዜ ወደ ሄሮድስ ሰደደው እርሱ ደግሞ በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም ነበርና:: ሄሮድስም ኢየሱስን ባየው ጊዜ እጅግ ደስ አለው:: ስለ እርሱ ስለ ሰማ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሊያየው ይመኝ ነበርና:: ምልክትም ሲያደርግ ሊያይ ተስፋ ያደርግ ነበር:: በብዙ ቃልም ጠየቀው እርሱ ግን አንድ ስንኳ አልመለሰለትም:: የካህናት አለቆችም ጻፎችም አጽንተው ሲከሱት ቆመው ነበር:: ሄሮድስም ከሠራዊቱ ጋር ናቀው:: ዘበተበትም፣ የጌጥ ልብስም አልብሶ ወደ ጲላጦስ መልሶ ሰደደው:: ሄሮድስና ጲላጦስም በዚያን ቀን እርስ በርሳቸው ወዳጆች ሆኑ ቀድሞ በመካከላቸው ጥል ነበርና።

በእውነት የገሊላው ንጉሥ ከኢየሩሳሌሙ መስፍን ጋር የቀደመ ጠባቸውን በንጹሕ ደም ትተው ከሰቃልያን ጋር በእግዚአብሔር መሲሕ ላይ አጉረመረሙ:: ሐዋርያት በመዝሙር ሁለት ትርጓሜ እንደ ተናገሩት:: አሕዛብ ለምን ያጉረመርማሉ? ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ? የምድር ነገሥታት ተነሡ፣ አለቆችም በእግዚአብሔርና በመሲሑ ላይ ሄሮድስና ጲላጦስ በእግዚአብሔር መሲሕ ላይ በእውነት አጉረመረሙ:: ስለዚህም የገሊላ ነገሥታት መንግሥት ተወገደ:: ከሳኦል እስከ ፍልሰተ ባቢሎን በጽዮን ቅባት ቀንድ ይሸ[illegible] ነበር:: [illegible] ጽዮን ምርኮ መመለስ ድረስ ያለ ንጉሥ፣ ያለ አለቃ፣ ያለ ካህንና ያለ ልብሰ ተክህኖ ሰባ አምስት ዓመት ተቀመጡ:: ከጽዮን ምርኮ መመለስ፣ በፋርስ ንጉሥ በዳርዮስ ዘመን በዘሩባቤል እጅ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በታነጸ ጊዜ የገሊላም መንግሥት ወደ ዳዊት ዘር ገባች:: የአሕዛብ ነገሥታት ይገዙአቸዋል እንጂ ሹመታቸው እንደ ቀድሞው በጽዮን ቅባት ቀንድ አይደለም:: ከለዳውያን የገዙአቸው ጊዜ አለ፣ ሚዶናውያን የገዙአቸው ጊዜ አለ፤ ሮማውያንም የገዙአቸው ጊዜ አለ:: እንግዲህ በምርኮ እስከ ገቡበት ጊዜ ድረስ መሲሐውያን አልተሾሙም::

በዝሙት ፍትወትና በደልን በማምጣት ሳይሆን፣ የሰውን ልጅ ጠባይ የሚገዛ መራራ የሞት ጽዋን በመጠጣት ለሥጋ ሕግ ተገዙ:: የሚያጠፉትን በማጥፋት አልተገዛላትም:: ጴጥሮስን ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይሞታሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ እንዳለው:: ወይስ አባቴን እንድለምን እርሱን አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይችል ይመስላችኋልን? እንዲህስ ከሆነስ እንደዚህ ሊሆን ይገባል:: የሚሉ መጻሕፍት እንዴት ይፈጸማሉ? ለጠባይ በሚገባ ገንዘብ ለሥጋ ሕግ ተገዛ:: ለቅዱሳን በማይገባ ገንዘብ እግዚአብሔርን በማያስቆጣ ገንዘብ አልተገዛለትም፣ ሁሉም ኃጢአት ከሥጋ አይደሉምና። የሥጋን ድካም ከሚገዛ ከሰይጣን እንጂ የኢየሱስ ድካም በሕገ ሥጋ እግዚአብሔርን በሚያሳዝነው ገንዘብ አይደለም:: ሥጋውም ኃጢአትን ለመሥራት አይደለምና፤ የሰይጣን ሥልጣን አይቀርበውምና:: ስለዚህ ጳውሎስ ኃጢአተኛን ሥጋ ለብሶ ይህችን ኃጢአት ገዛት አለ:: እግዚአብሔር ሰውነታችንን በመለኮቱ ያስተካክል ዘንድ ከእኛ ለእርሱ አደረገ:: የእርሱንም ኃይል ወደ እኛ ሥጋ መለሰው፤ ከእኛ ያለ ሩካቤ ሰው ሆኖ በንጽሕና ተሞሸረ:: ወንጌላዊው ዮሐንስ፦ «ቃል ሥጋ ሆነ፣ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ::» ብሎ እንደ ተናገረ፤ የዚህች ቃል ትርጉም ምንድነው? ዓይኖቻችሁ የጨለሙ. ጆሮቻችሁ የደነቆሩ ልባችሁ የጠፋ ሆይ በዚህም ትስታላችሁ? አስቀድሞ ሥጋ ከሆነ ከማርያም ሥጋዌን ለምን ወደደ? አንዱ የሚቀድም አንዱ የሚከተል ሁለት ሥጋዌ አለን? ሐሰት ነው የእግዚአብሔር ልጅ የሚገባው አይደለም:: ከማርያም በስተቀር ሰው አልሆነም::

ቃል ሥጋ ሆነ፣ በእኛ አደረ የሚለውን ነገር ሰሙ፤ እነግራችኋለሁ ቃል ሥጋ ሆነ ከቅድስት ድንግል ቃል ሥጋ በመባል ይተረጐማል:: በእኛም አደረ የሚለው የክርስቶስ ጸጋ በሐዋርያት ላይ ወደ ማደሩ ይተረጐማል:: ራሱ በወንጌል እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ እንዳለ:: ክርስቶስ የሚኖረው ከሐዋርያት ጋር ብቻ አይደለም በቃላቸው ካመኑበት ሁሉ ጋር እንጂ:: የሚወደኝ አባቴ ይወደዋል፤ ከእርሱ ጋር መጥተን በእርሱ ዘንድ ማረፊያ እናደርጋለን ብሎ ራሱ እንደተናገረ::

ሰነፎቹ ሆይ ክርስቶስ በድንግል ማኅፀን ሳያድር ሥጋ እንደለበሰ ዕወቁ፤ ነገር ግን ሥጋ ሳይሆን አስቀድሞ በሥጋውያን ልጅ ማኅፀን ውስጥ አድሮ ሥጋ ሆነ:: ያለ ወንድና ሴት ዘር ልማድ እናቱ ያለወንድ ዘርና ያለ ጽንስ ልማድ ትፀንስ ዘንድ አደረጋት:: ያም ምድራዊ አባት ከእርሷ ይወለድ ዘንድ አደረገ:: ወልድ ለአባቱ ብቸኛ ነው ወንድምና እኅት የለውም:: ስለ ልደቱም አኗኗር ከዚህ እስከዚህ የማይባል ነው:: በአባቱ ህላዌ ፀዳልና በአባቱ መልክ አርአያ የተገለጠ ነው:: በመንግሥት /ግዛት/ በክብር በመለኮት እኩል ትክክል ነው:: በኋለኛው ዘመን በራሱ ፈቃድ፣ በአባቱ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የተወለደ ነው:: ቃል ብቻውን፣ ብቻዋን ድንግል ከምትሆን፣ ኃይል ብቻውን ብቻዋን ምድራዊት ከምትሆን የተወለደ ነው፤ የማይዳሰስ እሳት ብቻውን የማይታይ መንፈስ ብቻውን ከብቻዋ ሴት ሰው የሆነ ነው:: አርዮስ ፍጡር ሊያደርገው ያሰበው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የአርዮስን ትምህርት የተከተሉ አርዮሳውያን ይባላሉ:: ንስጥሮስ ከነቢያት እንደ አንዱ ያሰበው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የእርሱን ትምህርት የተከተሉ ንስጥሮሳውያን ተባሉ:: አርጌንስ ከአባቱ ማነሱን ያስተማረበት እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የእርሱን ትምህርቱንም የተከተሉ አርጌሳውያን ተባሉ፤ መንኪዮስ ሥጋዌውን ምትሐት ያለው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የእርሱን ትምህርት የተከተሉ መንኪዮሳውያን ተባሉ:: አቡርዮስ በኑር ያለፈቃዱ ታሞ ሞተ ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ትምህርቱን የተከተሉ አቡርዮሳውያን ተባሉ:: አፍቲክስ ሥጋውን ከሰማይ አወረደ ያለው እርሱ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: አፍቶክስን ትምህርት የተ

መናፍቃን በሥጋና በነፍስ ወደ ሲኦል ወረደ ያሉት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የእርሱን ትምህርት የተከተሉትም አርሲሳውያን ተባሉ:: አርሲሳውያን ማለት ከሃድያን ማለት ነውና:: ከዘከርናቸው እንደ አንዱ የሰው ስም አይደለም:: ልዮን ትሰብእቱ ከመለኮቱ ያንሣል ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የእርሱም ትምህርት የተከተሉ ልዮናውያን ተባሉ:: የኪልቄዶን ማኅበር የመለኮት ሥራ ለመለኮት ይገባል የትስብእት ሥራ ለትስብእት ይገባል ብለው ለሁለት ባሕርይና ለሁለት ሥርዓት የከፈሉት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ዳግመኛም አንዱ ተአምር ያደርጋል አንዱም ሕማም ይቀበላል ይላሉ:: ትምህርታቸውን የተከተሉት መለካውያን ተባሉ:: የሃይማኖታቸው ፍላጐት በንጉሥ ዘንድ ሁኗልና:: ንጉሡ መርቅያን የልዮንን ሃይማኖት ወዷልና:: ስለዚህ በኒቅያ ከተሰበሰቡት ከ፫፻፲፰ ማኅበር ማኅበራቸው የበለጠች ትሆን ዘንድ ለረከሰች ሃይማኖቱ ክብር ፈልጎ ፮፻፴፮ ኢጲስ ቆጶሳትን ሰበሰባቸው:: ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በእነርሱ ይመኩባቸዋልና፤ የክህደት መምህር በስሙ ያሳሳታቸው ሁሉም ከሃድያን ይባላሉ::

እኛ ግን ከእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አፀድ የሚያስወጡ መምህራንን አንፈልግም፤ ዳግመኛም በስማቸው መጠራትን አንፈልግም:: መምህራችን ክርስቶስ ለራሳችሁ መምህር አትሹሙ መምህራችሁ አንዱ ክርስቶስ ነው ይለናልና:: ስለዚህም ክርስቶስ ተብሎ እንደ ተጠራ እኛም ክርስቲያን እንባላለን:: መሲሕ እንደተባለ መሲሐውያን እንባላለን:: ናዝራዊ እንደ ተባለ ናዝራዊያን እንባላለን:: የእነዚህ የሦስቱ መጠሪያዎች ትርጉም በአንድ የተቀባና የተቀቡ ተብሎ ይተረጐማል::

ከእነዚህም መናፍቃን የወልድ ሥጋ በአብ ቀኝ አልተቀመጠም የሚሉ አሉ ሰነፎች ምክር ያጣችሁ ሆይ ሥጋው በአብ ቀኝ አልተቀመጠም ትላላችሁን? ስለምን ዳዊት እግዚአብሔር ጌታዬን ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው? አብ በቀኜ ተቀመጥ ያለው ስለ ወልድ መለኮት ትላላችሁን? የወልድ መለኮት በአባቱ ቀኝ ለመቀመጥ መቼ ተስማማ? የሰው ልጅ ለመሆን ቢጨነቅም እግዚአብሔርነቱን አልተወም፤ በድንግል ማኅፀን ሕፃን በሆነም ጊዜ በጽርሐ አርያም ከአባቱ ጋር ሽማግሌ ነው:: ገሊላዋት እናቱም በክንዶቹ በታቀፈችው ጊዜ

www.ethiopianorthodox.org

በኪሩቤል ሰረገላ ላይ ነበር። በሕፃናት ሥርዓት የጡቶቿን ወተት በጠባም ጊዜ በአምላክ ሕግ ከአባቱ ጋር ሕልው ነው። በዮርዳኖስ ውስጥ ለመጠመቅ እርቃኑን ሲገለጥ በላዩ ላይም በብርሃን ድንኳኖችና በመብረቅ ክብር የተጨመረበት በደመና መጋረጃዎች ይሰወራል። አብ በዮርዳኖስ ወንዝ ምስክር ሲሆን መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ሲጐበኘው ያለ ሥጋዌ ከእነርሱ ጋር ሲሰለስ ያን ጊዜ በመገለጫቸው ቦታ ነበር። በጭፍሮች ተገርፎ በጲላጦስ አደባባይ ፊት በቆመም ጊዜ በሰማየ ሰማያት የሚካኤል ሠራዊት በፍርሐትና የገብርኤል ሠራዊት በመንቀጥቀጥ ከፊቱ ቆመው በሰማያዊ አባቱ ቀኝ ሕልው ነው። የካህናት አለቆች፣ የሕዝብ ጽሑፎች፣ በመንገድ የሚተላለፉ መንገዶች፣ ሲሰድቡትና ሲያንጓጥጡት ከበላዩ ኪሩቤል እያመሰገኑት ሱራፌል እየቀደሱት ሕልው ነው። በመስቀል ላይ በቅንዋተ መስቀል ተቸንከሮ እጆቹንም በዘረጋ ጊዜ እንደ አብና መንፈስ ቅዱስ ሕልው ነው። መለኮቱ ሳይነካ ሕልው ነው በሥጋ ሞትን በተቀበለ ጊዜ መለኮቱ በመቃብር ውስጥ ከበድን ሥጋው ጋር ያለ ነፍስ ወደ ሲኦል ውስጥም ከነፍሱ ጋር ያለ ሥጋ በአባቱም ቀኝ ያለነፍሱና ሥጋው ህልው ነው። በትንሣኤውም ጊዜ ነፍሱን ወደ ሥጋው ማኅደር በመለሳት ጊዜ አስቀድሞ ለአይሁድ ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤ ከሦስት ቀን በኋላ አነሣዋለሁ።» እንዳላቸው አይሁድ ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር። ስለዚህ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደተናገረ አሰቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ።

ዳግመኛ ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ፣ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ። ዳዊትም አቤቱ አንተና የመቅደስህ ታቦት ወደ ዕረፍትህ ተነሥ አለ። ነቢዩ ስለምን አቤቱ አንተና የመቅደሱ ታቦት ተነሥ አለ? ይህችውም የመቅደሱ ታቦት ከሆነች ከዳዊት ዘር ከነሣው ሥጋ ጋር በመለኮቱ ኃይል ከእንቅልፍ ሞት ከመነሣት ነው? ምድራዊ ድካም ወዝ፣ ድካም፣ ረኃብ፣ መጠማት፣ ደዌና ሕማም ከሌለባት ከጽርሐ አርያም በስተቀር ዕረፍት ምንድንነው? አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ የሚለው ቃል የሞት ሥልጣን አይቀርብህም ሰቃልያን አይደርሱብህም ወደሚለው ይተረጐማል። አንተ የመቅደስህ ታቦት የሚለው ቃል ለመለኮትህ ኃይል ማደሪያ የሆነች ሥጋዌህና አንተ እግዚአብሔር ወደሚለው ይተረጐማል።

እነሆ የመዝሙሩ ቃል ትስብእትን ስቧት ከመለኮቱ ጋር እስከ ጽርሐ አርያም ከፍ ያደርጋታል። የመለኮት ትስብእት ግን በመዘምራን ዘንድ ታቦትን ተመሰለች። አቤቱ አንተና የመቅደስህ ታቦት ተነሡ ይላልና፤ በሰሎሞን ዘንድም መሸከሚያ ነው፤ ንጉሥ ሰሎሞን መሸከሚያ ምሰሶዋን ከሊባኖስ እንጨት ለራሱ አሠራ ይላልና የመድኃኒታችን የትስብእቱ ምሰሶዎች አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብና የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት ናቸው። የቤት ማዕዘን በአራት ማዕዘን እንደሚጸና የእግዚአብሔር የኪዳኑ ትስብእት በአብርሃም እምነት በይስሐቅ ጽንዓት፣ ቢያዕቆብ ምሥጋናና በዳዊት የአምልኮት መልክ በአራቱ የማዕዘን ምሰሶዎች ጸንቶአል። ስለ ዚህም ወንጌላዊው የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ አለ። የእግዚአብሔር ኪዳን ባለበት ጀምሮ በባዕዳን ትውልድ አስከተሎ ይህን ቃል በመከተል መቀመጫውን ሐምራዊ ግምጃ አደረገ አለ። የድንግል ማርያም የሥጋዋ ጽዳት እንደ ሐምራዊ ግምጃ ነውና የሔዋን የበደል እሾክና የአዳም የኃጢአት እሾክ በውስጧ አልበቀለምና ከዚህም በኋላ ውስጡ በሰንፔር ድንጋይ የተነጠፈ ነው አለ። የሰንፔር ድንጋይ በፍህም ብዛት ይቀላልና ይህም የመለኮቱ አምሳል አርአያ ነው።

ሕዝቅኤል እንዳለው እንደተናገረው በእነዚህ የሰማይ እንስሳት በራሳቸው ላይ በላዩ ላይም እንደ ሰንፔር ዕንቁ ያለ የበረድ ኅብር የተዘረጋ ነው። የጸናች አራት የእስራኤል ልጆች ከእግሩ ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱ፤ በሦስት ቀን አነሣዋለሁ ይላልና ወንጌላዊ። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይነግራቸው ነበር አለ። መጋረጃ ትስብእት ትባላለች ጳውሎስ በሥጋው መጋረጃነት በድንገት የሕይወትንና የጽድቅ መንገድን አድሶልናልና ይላል ትስብእት ታቦት ትባላለች። በመዘምራን አፍ የመለኮት ሙዳይ ስለሆነች በክብር ከእርሱ ስላሳነሰች በአብ ቀኝ ተቀምጣለችና በተዋሕዶ እንጂ በመንታነት /በምንታዌ/ አይደለም። በሥጋ እግሮች በዓለም ውስጥ እግዚአብሔር ስለተመላለሰ ትስብእት መሸከሚያ ትባላለች። በኪሩቤል ሰረገላ ስለተቀመጠች ከእርሱ በክብር አታንስም። የኃይል ቤት ስለሆነች ከእርሱ በብርሃንና በፀዳል ሳላልጐደለች ትስብእት ቤተ መቅደስ ትባላለች። በደመና እሳት ከፍ ብላ የሰውና የመላእክት አእምሮ ወደ ማይደርስበት ወደ ጽርሐ አርያም ገብታለችና። ለማይታይ ኃይል መሠወሪያ ስለሆነች በአምልኮት መልክ ክብር ከእርሱ ስለማታንስ ትስብእትም መጋረጃ ትባላለች። በሰማየ ሰማያት ሲያዩት የሚያስፈራ የእሳት መጋረጃ ተዘርግቶላታልና።

ጌታ ጌታዬን ጠላቶችን የእግርህ መረገጫ እስከ ማደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ ወዳለው ወደ ዳዊት ቃል ነገር መንገድ እንግባ። ያልነበረ የወልድ ትስብእት ይቀመጥ ዘንድ ስለ ወልድ ትስብእት አብ ይህን አለ። የተቀመጠውን ግን ተቀመጥ አይሉትምና፤ የእግዚአብሔር ልጅ የመለኮቱ ሕልውና የተቀመጠ ነውና። ከአባቱ ሕልውና መቼም አልተለየም፤ በወላጁ ቀን ለዘላለም ይኖራል። ስለ መለኮቱም ትስብእት ግን ከልደቱ ዕለት እስከ ዕድገቱ ፍፃሜ ድረስ የሕፃናትን ሥርዓት ፈፀመ ከዕድገቱ ፍጻሜም እስከ ስቅለቱ ዕለት የጉርምስና ሕግን ከኃጢአት ብቻ በስተቀር ሳያተርፍ ፈፀመ። በስቅለቱም ዕለት የአባቱን ትእዛዝ ፈጸመ። ለምእመናን ክብር ይሰጥ ዘንድ መከራን ለበሰ መከራን ጻዕርን ሥቃይን ሐፍረትን ለሚታገሱ ሰማዕታት ፍለጋውን ይተው ዘንድ ለብዙኃንም ቤዛ ይሆን ዘንድ የመስቀልን ሐፍረት ታገሰ። ኢየሩሳሌም የቀዳችለትን የሞት ጽዋ ጠጣ። በሰው ሕግ ላይ ሰልጥኖ በመለኮቱ ኃይል ተነሣ በተነሣበት በእሑድ ንጋትም አስቀሞ ለመግደላዊት ማርያም ታያት። እሱ ጌታ ኢየሱስ እንደሆነ ባወቀችው ጊዜ እግሩን ትስመው ዘንድ ወደደች ወደ አባቴ ገና ዐላረግኩምና አትንኪኝ አላት። በመንገድ ባገኘችው ጊዜ ወደ አባቴ ገና ዐላረግኩ

በኋላ እሱን መንካት እንዴት ይቻላል? ከሰው ልጅ ወደ ሰማይ ማረግ የሚችል የለምና።

ስለምን አትንኪኝ አላት? ዘማዊቷ ሴት፣ በፀጉሯ የዳሰሰቻው፣ በእንባዋ እግሮቹን ያጠበችው የዳሰሰችው እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን? ደም ይፈሳት የነበረችው ሴት የዳሰሰችው በመለኮቱ ኃይል ደሟን ያደረቀላት እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን? ጸሐፍት ፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርቱን መምህራችሁ ለምን ከኃጢአተኞችና ከቀራጮች ጋር ይቀመጣል? ብለው እስከ ሚያንጐራጉሩ ድረስ ዘወትር ከኃጢአተኞች ጋር የሚቀመጥ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን? በምራቁ ወደ ምድር ተፍቶ ዓይኖቹን ቀብቶ አስቀድሞ ዓይን ላልነበረው ሰው ዓይን የፈጠረ፤ እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን? በብረት ዘንግ ራሱን መትተው በፊቱ ላይ ርኩስ ምራቅን የተፉበት እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን? ከእርሷ ሰባት አጋንንትን ያስወጣላትን ማርያም መግደላዊትን ዘወትር የሚወዳት እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን?

ከትንሣኤው በኋላ ስለምን አርቋት አትንኪኝ አላት? ትርጉሙን እንናገር፤ እስከ ሞተበት ጊዜ ድረስ በትስብእቱ መከራ የአባቱን ፈቃድ ፈጸመ። ወንጌላዊው እንደ ተናገረው ሐሞቱን ጠጥቶ ሁሉ ተፈጸመ አለ። በትንሣኤውም ባለፈው የትስብእት መከራና በሚመጣው የክብር ክብር በመለኮቱ ክብር በተሳተፉ መካከል ለየ።

እንደ ንጉሥ ልጅ በመንግሥት መንበር ከመቀመጡ በፊት የአባቱ አሽከሮች እንደ ወንድምና ጓደኛ ይቀልዱበታል። እርሱም ራሱን ከእነርሱ እንደ አንዱ አድርጐ በፍቅርና በትሕትና ይቀበላቸዋል። በአባቱ መንበር እንደ ተቀመጠም በፊቱ ይሰግዳሉ። ማንም እንዳይቀርበው የማያስገቡ ጠባቂዎች በፊቱ ቆመው እንዳይነኩት በፊቱ ይሰግዳሉ። ከእርሱ ጋር ከሚጠጉ ንጉሥም ከሚቀመጥባቸው ከሚቀርባቸው በስተቀር እርሱን መንካት የሚችል የለም። በመኃልይ መኃልየ ባለ ብር ጉብጉብ የሆነ የወርቅ ጠልስም እናደርግልሻለን፤ ንጉሡ በማዕዱ ሳለ እንደተባለው ይህም ማለት በአባቱ ሕል

www.ethiopianorthodox.org

የነበረ ንጉሥ በሥጋዌው ከንጉሥ ዳዊት ዘር
ኢየሱስ ክርስቶስ በማዕዱ እስከሚቀመጥ
ድረስ ቀሳውስትንና ኢጲስ ቆጶሳትን ለአንቺ
ይሾማሉ ማለት ነው:: የንጉሥ ሠራዊት
መቅረብን እንደማይችል በእርሱ ዘንድ ቀር
በው ሥልጣንን አይቀበሉምና:: እንዲሁ ሕዝ
ባውያን ወደ ጽንሐው ምስጢር ቀርበው
ሥጋወ ደሙን ለመዳሰስ አይችሉም:: ስለዚ
ህም መግደላዊት ማርያምን አትንኪኝ አላት::
ሥጋውን ካለፈው የትስብእት መከራ ከል
ከሏልና በተነሣም ጊዜ ከመለኮቱ ክብር
አሳተፉት::

የንጉሡ ቤት ጠባቂዎች ንጉሡን ይቀር
ቡትና ይነኩት ዘንድ እንደሚገባቸው እን
ዲሁ ኤጲስ ቆጶሳትም ካህናትም የክርስ
ቶስን ቀርባን ሥጋውን ይነኩ ዘንድና ጣታ
ቸውን ወደ መለኮቱም ደም ውስጥ ይነክሩ
ዘንድ ይገባቸዋል:: በተነሣበት በዕለተ እሑድ
ሐዋርያቱን አስቀድሞ አሰልጥኖአቸዋልና::
ለምን ልባችሁ ውስጥ ሐሳብ ይገባል? ምንስ
ያስደገንጣችኋል? እኔ እንደሆንኩ እግሮቼ
ንና እጆቼን ዳሳችሁ እዩኝ አላቸው:: መግ
ደላዊት ማርያምን በትንሣኤው ንጋት አት
ንኪኝ አላት፤ ሐዋርያቱንም በትንሣኤው
ማግስት ዳሱኝ አላቸው:: መግደላዊት ማር
ያምን ትታቀብ ዘንድ በምእመናንና በም
እመናት ሥርዓት ጠቀሳት:: ሐዋርያትን
ለምሥጢር ካህናት አርአያ ይሆኑ ዘንድ
ሥጋውን ይዳስሱት ዘንድ አሰለጠናቸው::

በዚህም ከትንሣኤው አስቀድሞ መለኮት
የትስብእትን መከራ እንደ ተሳተፈ ዝንጉዕ
ሆይ አስተውለህ ዕወቅ:: ከትንሣኤውም በኋላ
ግን ትስብእት የመለኮትን ክብር እንደተ
ሳተፈ ዕወቅ:: በዕሪና ሳይከፈል በተዋሕዶ
ሳይለወጥ ነግሦ ታየ:: ለመጀመሪያው ሄሮ
ድስና ለሁለተኛው ሄሮድስ ምድራዊ መን
ግሥታቸው እሱ እንደሚወስድ መሰላቸው::
ቀዳማዊው ሄሮድስም ከተገደሉት እንደ
አንዱ ያገኝ ዘንድ እርሱን ፈልጐ ሕፃናትን
ገደላቸው:: ሁለተኛው ሄሮድስ በተሰቀለበት ዕለት
አክፋፍቶ ወደ ጲላጦስ ዘንድ እሱ መንግ
ሥቱን እንደሚፈልግ ታዝቦት በእርሱ ላይ
ስሳለቅ ይቅር ያለውን ቀይ ከለሜዳ አል

አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን? ብሎ ጠየ
ቀው እርሱም መልሶ አንተ የምትለው ከልብህ
ነውን ወይስ ሌላ ሰው የነገረህን አለው::
ጲላጦስም መልሶ እኔ አይሁዳዊ ነኝን? ሕዝ
ብህና የካህናት አለቆች ወደ እኔ አሳል
ፈው የሰጡህ አይደለምን? አለው:: ጌታ
ኢየሱስም መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደ
ለችም:: መንግሥቴ ከዚህ ዓለም ቢሆን
ግን አሽከሮቼ አይሁድ ከአንተ ዘንድ አሳ
ልፈው እንዳይሰጡኝ በተዋጉልኝ ነበር አለው::

የእግዚአብሔር ልጅ የአባቱን የዳዊት
መንግሥትን ንቋት እስከ ትንሣኤው ድረስ
በችግር ተቀመጠ ከትንሣኤው በኋላ በመ
ለኮት ክብር ከልሏት በአባቱ ቀኝ አስቀ
መጣት:: ከዚህም በኋላ ከዳዊት ዘር የገሊላ
መንግሥት ተወገደች:: ያዕቆብ በትረ መን
ግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፤ የገዥም ዘግን
ከእግሮቹ መካከል ገዥ የሆነው እስኪመጣ
ድረስ የአሕዛብ ተስፋቸው ነው:: እንዳለ
ከይሁዳ ገዥ አይጠፋም የተባለው ከልጁ
ከተወለደው ከኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር
ምንድን ነው? በሐዋርያት እጅ ለአሕዛብ
ከተሰጠ ከእግዚአብሔር ልጅ ጸጋ ከወንጌል
በስተቀር የአሕዛብ ተስፋ ምንድን ነው?

እኛ ግን ሐዋርያት ስለሰበሰቧት ስለ አን
ዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላም ዳግ
መኛ እንማልዳለን እንላለን እነርሱም የአሕ
ዛብ የሆነችው ያቺ ቤተ ክርስቲያን የተ
ባረከች ናት ይሏታል:: ሃይማኖታችንን በሃ
ይማኖታቸው ለጨመረ ለእግዚአብሔር ለዘ
ላለም መሥጋና ይሁን አሜን::

የሮማውያንን ትምህርት ያጠፋና እንደ
ሰይጣን ለማሳት የሚጨነቅ እንደ ሌጌዎን
አጋንንት ለማጣደፍ የሚተጋ ከግዮን ወንዝ
አፍ አሸዋ የሚበዛ የመርቅያን የስንፍና መም
ህር የልዮን ዘለፋ ተፈጸመ::

ከተቀራረቡ ተራሮች መሠረትና ከማይ
ንቀሳቀሱ ተራሮች ሚዛን የኃጢአቱ ክብደት
የሚበልጥ ጊዮርጊስ እለ ተናገረ:: ለእግዚአ
ብሔር ለዘላለም ምሥጋና ይሁን አሜን::